የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
City Government of Addis Ababa
Ethics and Anti-corruption Commission

# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# የቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ የሰራተኞች የሥነ ምግባር መመሪያ ቁጥር 4/2016

የካቲት 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ የአዲስ አበባ ቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ የሠራተኞች የሥነ ምግባር መመሪያ ቁጥር 4/2016 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

1. **"ቢሮ"** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ ነው፡፡
2. **"ሠራተኛ"** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 56/2010 መሰረት በቢሮው በዳይሬክተርነት፣ በቡድን መሪነት፣ በባለሙያነት በቋሚነት ተቀጥሮ በመስራት ላይ ያለ፣ በሙከራ ጊዜ ወይም በጊዜያዊነት ተቀጥሮ በመስራት ላይ የሚገኝ የተፈጥሮ ሰው ነው፡፡
3. **"ሐብት"** ማለት ማንኛውም የማይንቀሳቀስ ወይም የሚንቀሳቀስ ወይም ግዙፍነት ያለው ወይም የሌለው ንብረት ማለት ሲሆን የመሬት ይዞታንና ዕዳን ይጨምራል፡፡
4. **"የጥቅም ግጭት"** ማለት ማንኛውም ሠራተኛ ከሚያከናውነው ሥራ ጋር በተያያዘ ማናቸውንም የሥራ ግንኙነት በመፈጸም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እራሱ ወይም ከእርሱ ጋር በዝምድና፣ በገንዘብ ጥቅም፣ በትውውቅና በጥቅም ትስስር ግልፅ ተቃርኖ እንዳለ ተዓማኒነት ባለው ማስረጃ ሲረጋገጥ አለመጣጣም መኖር ነው፡፡
5. **"ሥነ ምግባር"** ማለት በቢሮ ውስጥ የሚገኙ ሠራተኞች ከሚያከናውናቸው የዕለት ተዕለት ተግባራት ጋር በተገናኘ ከሥራ ባልደረቦቻቸው፣ የቢሮን አገልግሎት ከሚፈልጉ የመረጃ ተጠቃሚዎች ወይም ደንበኞች ጋር ባላቸውና በሚኖራቸው ግንኙነቶች እንዲሁም መስተጋብሮች (Relations & Interactions) በተግባርም ሆነ በቃል ሊያሳዩና ሊያንጸባርቁት የሚገባ መልካም የሆነ የሥራ ባህሪይ፣ ባህል፣ አስተሳሰብ፣ አመለካከትና የመሳሰሉትን ነው፡፡
6. **"መስተንግዶ"** ማለት የቢሮ ሠራተኛ በሥራው ላይ ተፅዕኖ ሊያደርግበት የሚችል ነፃ የሆነ የምግብ፣ የሆቴል ወይም የምግብ ቤትና የመሳሰሉት አገልግሎቶችን የሚመለከት ነው፡
7. **"ሥነ ምግባር ብልሹነት"** ማለት በቢሮ ውስጥ የመልካም ሥነ - ምግባር መርሆዎችን የሚቃረን ተግባር መፈጸም፣ መልካም ያልሆነ ባህሪይ፣ አስተሳሰብ፣ አመለካከት ይዞ መገኘትና ይህንኑ በድርጊት መግለፅ ነው፡፡
8. **"ኮሚሽን"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ የሥነ ምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ነው፡፡

2. የጥቅም ግጭት ሊከሰት እና ሊወገድ የሚችልበትን ሁኔታ ለመጠቆም፤
3. ሠራተኛው የቢሮውን ንብረትና ሐብት በባለቤትነት ስሜት እንዲጠብቅ እና እንዲንከባከብ ብሎም የሥነ ምግባር ግድፈት እንዳይፈፀም ለመከላከል እንዲችል፣ ሲፈፀም ሲያይም እንዲጠቁም ለማስተማር እና ለማበረታታት፣
4. ሠራተኛው መብትና ግዴታውን አውቆ በሕግ፣ በደንብና በመመሪያ መሠረት ሥራውን እንዲያከናውን ለማድረግ፣
5. በቀልጣፋና ደንበኛ ተኮር አገልግሎት አሰጣጡ ቢሮው በደንበኞቹ ዘንድ እምነት የሚጣልበትና የተከበረ ተቋም እንዲሆን ለማስቻል፤
6. የሥነ - ምግባር ግድፈት ሲፈጸም የእርምት እርምጃ መውሰድ የሚቻልበትን ስርዓት ለማጠናከር፤
7. የቢሮው እና የተጠሪ ተቋማት ሠራተኞች የሥነ ምግባር መርሆዎችን ተከትለው መደበኛ ሥራቸውን እንዲሠሩ ለማስቻል ነው፡፡

## ክፍል ሁለት
## መሠረታዊ የሥነ ምግባር መርሆዎች

### 6. የሥነ ምግባር መርህ ምንነት

የሥነ ምግባር መርህ በቢሮ በዕለት ተዕለት የሥራ እንቅስቃሴ ውስጥ ጥሩና መጥፎ፣ መደረግ ያለበትና የሌለበት ድርጊት የሚገለጽበት፣ አጠቃላይ የአስተሳሰብ፣ የአመለካከት እና የተግባር አፈፃፀሞች የሚመሩበት ስርዓት ነው፡፡

### 7. ሐቀኝነት

ሐቀኝነት ማለት በቢሮው መደበኛ የአሠራር ስርዓት ውስጥ እውነተኛ መሆን፣ ከማጭበርበር፣ ከማታለል ብሎም በስልጣን ያለአግባብ ከመገልገል መራቅና የሙያ ነፃነትን ጠብቆ ፍትሐዊ አገልግሎት መስጠት፣ ተገልጋዮችን በማጉላላት ለአላስፈላጊ ድርድር በሚያመች ሁኔታ የሙያ ተግባርን አለመፈፀም፣ መልካም ሥነ - ምግባር በማሳየት ሥራን በሙያዊ ብቃት፣ ክህሎት፣ በሙሉ ጉልበት እና በጥንቃቄ ማከናወን መቻል ማለት ነው፡፡ በመሆኑም፡-

1. ማንኛውም የቢሮው ሠራተኛ፡-
   ሀ. የቢሮን መልካም ስምና ዝና የሚጎዳ ወይም ተገልጋዮች በተቋሙ ላይ ያላቸውን አክብሮትና እምነት ዝቅ የሚያደርግ ባህሪ ከማሳየት መቆጠብ ወይም ለመልካም ሥነ ምግባር ተቃራኒ ከሆነ ድርጊት ራስን ማራቅ፤

1. ማንኛውም የቢሮ ሠራተኛ፡-
   ሀ. መደበኛ ሥራን ቢሮ ያወጣቸውንና የሚያወጣቸውን መመሪያዎች ወይም ማንዋሎች መሠረት በማድረግ ማከናወን፤

   ለ. የሥራ ባልደረባና ሌሎች ሰዎች በቢሮ ላይ የሚፈፅሙትን ወይም ሊፈፅሙ ያሰቡትን የህገ - ወጥ ድርጊት አዝማሚያ፣ የሥነ ምግባር ጉድለት ወይም ተገቢ ያልሆነ አድራጐት ለቅርብ የሥራ ኃላፊ ወይም ለሥነ ምግባር መኮንን ማሳወቅ፤

   ሐ. በቢሮ የሥራ ሰዓት የግል ወይም የሌላ ሰው ጥቅም ሊያስከብር የሚችል ሥራ አለማከናወን፤

   መ. በሥራ ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን ለቅርብ የሥራ ኃላፊ በወቅቱ ማሳወቅ፤

   ሠ. የሥራ ባልደረባና ሌሎች ሰዎች በቢሮ ላይ የሚፈፅሙትን ወይም ሊፈፅሙ ያሰቡትን የህገ - ወጥ ድርጊት አዝማሚያ፣ የሥነ ምግባር ጉድለት ወይም ተገቢ ያልሆነ አድራጐት ለሚመለከተው አካል ቅን ልቦናን በሚቃረን ሁኔታ ጥቆማ አለማቅረብ፤

   ረ. በተደጋጋሚ ያለበቂ ምክንያት ከቢሮ ቢሮ በመዘዋወር ሌሎች ሠራተኞችን ሥራ ማስፈታት ተጠያቂነትን እንደሚያስከትል መረዳት፤

   ሰ. አግባብነት የሌለው የግል ጥቅም ማግኘትን ወይም ለሌሎች ማስገኘትን ታሳቢ በማድረግ ቢሮ በሚያወጣቸው የግዥ ወይም የሽያጭ ጨረታዎች ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተሳታፊ ሆኖ መገኘት በሕግ እንደሚያስጠይቀው መገንዘብ ይጠበቅበታል፡፡

2. መርሆውንና በመርሆው ሥር የተደነገጉትን መተላለፍና የሚከተሉትን ጥፋቶች ፈጽሞ መገኘት ያስጠይቃል ወይም የእርምት እርምጃ ያስወስዳል፡-
   ሀ. የቢሮን ተሽከርካሪዎችና ሌሎች ንብረቶችን ላልተፈቀደ ዓላማ ማዋል፤

   ለ. ሕገ ወጥ የሆነ ትዕዛዝ መፈፀም፣ በሥራ ኃላፊ ሕገ ወጥ የሆነ ትዕዛዝ እንዲፈፅም የታዘዘ ሠራተኛ ይህንኑ ድርጊት ለቢሮ ኃላፊ ወይም እና ለቢሮ ጽ/ቤት ኃላፊ ወይም ለም/ቢ/ኃላፊ ወይም ለሥነ ምግባር መኮንን ያለማሳወቅ፤

   ሐ. የቢሮን ልዩ ልዩ ማህደሮች፣ ሰነዶችና ማስረጃዎች መደበቅ፣ መሰረዝ፣ መፋቅ፣ ማጥፋት ወይም መደለዝ፣ የቢሮን መልካም ስም ማጉደፍ ወይም አርማና ማህተም ለሕገ - ወጥ ድርጊት መጠቀም፤

   መ. ከቢሮ የበላይ ኃላፊዎች ወይም ከቅርብ የሥራ ኃላፊ የተላለፈን ሕጋዊ ትዕዛዝ አለማክበር፡

ሀ. በሥራ ግምገማ ወቅት አግባብነት ያለው አካል ላቀረበለት የመረጃ ጥያቄ በወቅቱ ምላሽ ለመስጠት ፍቃደኛ አለመሆን፤

ለ. ማንኛውም የሚመለከተውን ውሳኔን ወይም አገልግሎትን ያለበቂ ምክንያት ማዘግየት ወይም በስታንዳርድ መሠረት አለማከናወን፤

ሐ. ሕጋዊ ለሆነ ጥያቄ በእጅ ላይ የሚገኘውን ሚስጢር ያልሆነንና ለተገልጋይ ግልጽ እንዳይደረግ ያልተከለከለን መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆን ወይም በመደበቅ ማንኛውም አካል ለሚያቀርበው ጥያቄ በወቅቱ ግልጽ ምላሽ አለመስጠት፣ የተሳሳተ መረጃ መስጠት፣ ስለጉዳዩ ማብራሪያ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን፤

መ. ከሥራው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው አካል መረጃ መስጠት እየቻለ የማይመለከተው ሠራተኛ መረጃ መስጠት፤

ሠ. በሥራ አጋጣሚ በእጅ የገባን የቢሮን መረጃ ለግል ጥቅም፣ ለቂም በቀል ማዋል ወይም ለማዋል መሞከር፡፡

10. <u>ሚስጢር መጠበቅ</u>

ሚስጢር ጠባቂነት ማለት የቢሮን፣ የባልደረባን፣ የደንበኛን ወይም ጉዳዩ የሚመለከተውን አካል ጥቅም፣ መልካም ስም፣ ስብዕና ለመጠበቅ ወይም ጉዳት እንዳይደርስበት ለመከላከል ሲባል በሕግ ወይም በሚመለከተው አካል የተደነገጉ መረጃዎችን ወይም የውሳኔ ሀሳቦችን ይፋ ያለማውጣት፣ ለሌላ አካል ያለመግለጽ፣ አሳልፎ ያለመስጠት ወይም ለግል ፍጆታ ጥቅም ላይ ያለማዋል ማለት ነው፡፡ በመሆኑም፡-

1. ማንኛውም የቢሮ ሠራተኛ፡-

ሀ. በስራ ምክንያት ያወቀውን ወይም ያገኘውን የተቋሙን፣ የተቋሙን ሠራተኞችና ደንበኞችን የሚመለከቱ መረጃዎች ለተቋሙ ሥራ ብቻ ጥቅም ላይ እንዲውል ከማድረግ በስተቀር የእነዚህን ጥቅምና መልካም ስም ሊጎዳ በሚችል መልኩ ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት የመረጃዎቹን ይዘት ለሌላ ወገን መግለጽ፣ ቅጅውን አሳልፎ መስጠት፣ ማሳየት ወይም ይፋ ማድረግ የለበትም፤

ለ. ቢሮን ከለቀቀ ወይም በዝውውር ወደሌላ ቦታ ከሔደ በኃላ በስራው ምክንያት ያወቃቸውን ሚስጢራዊ መረጃዎች የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡ ሆኖም ጥፋትን ለማጋለጥ ለሚመለከተው ሕጋዊ አካል ሚስጢራዊ መረጃን ማሳወቅ ወይም መስጠት እንደሚስጢር ማባከን አይቆጠርም፤

ሐ. ተገልጋይ በቢሮ ላይ ያለውን አክብሮትና እምነት ዝቅ የሚያደርግ ባሕሪይ አለማሳየት ወይም ድርጊት አለመፈጸም፤

መ. መልካም ሥነ - ምግባር በማሳየት ሥራን በከፍተኛ ሙያዊ ብቃት፣ ጥንቃቄ፣ ጥራት፣ ስታንዳርድ እና ትጋት መሠረት ማከናወን፤

ሠ. ከሥራ ባልደረባ ጋር የሚኖር ግንኙነት ስራን ማዕከል ያደረገ፣ መማማርንና ማሕበራዊ ግንኙነትን የሚያጠናክር መሆን ይኖርበታል፡፡

2. መርሆውንና በመርሆው ሥር የተደነገጉትን መተላለፍና የሚከተሉትን ጥፋቶች ፈጽሞ መገኘት ያስጠይቃል ወይም የእርምት እርምጃ ያስወስዳል፡-

ሀ. ቅን ልቦናን በሚቃረን ሁኔታና ሠራተኛን ወይም ሌሎች አካላትን በሚጎዳ መልኩ ሐሰተኛ ጥቆማ ማቅረብ፤

ለ. የቢሮን ዝና የሚጎዳ ወይም ደንበኛው በመስሪያ ቤቱ ላይ የሚኖረውን እምነት ዝቅ የሚያደርግ ባሕሪ ማሳየት ወይም በተግባር መፈጸም፤

ሐ. በሥራ ቦታ አደንዛዥ እፅ (ጫት፣ ሲጋራ ወዘተ) መጠቀም፣ አልኮል ጠጥቶ መግባት፣ አምባጓሮ መፍጠር፣ በሥራ ላይ እንቅፋት መሆን፣ የሥራ ባልደረባን ቅንነት በጐደለው መልኩ በመረዳት የአሉባልታ ዘመቻ ማካሔድ ወይም ሐሜትን ማስፋፋት፡፡

## 12. <u>ተጠያቂነት</u>

ተጠያቂነት ማለት የቢሮ ሠራተኛ በተናጠልም ይሁን በቡድን በቢሮ ውስጥ በሚያደርገው ወይም ባደረገው ማንኛውም ዓይነት ሥራ፣ ውሳኔ፣ እርምጃ፣ ድርጊት ወዘተ በሚመለከተው አካል የመጠየቅ፣ በጉዳዩ ዙሪያ ማብራሪያ የመስጠትና ለሚደረግበት ተገቢ ለሆነ ምርመራ ዝግጁነትን ማሳየት ወይም ኃላፊነትን መውሰድ ማለት ነው፡፡ በመሆኑም፡-

1. ማንኛውም የቢሮ ሠራተኛ፡-

ሀ. ስለተከናወኑ ስራዎች እንደየስራው ባሕሪ ወይም ፀባይ መሠረት በማድረግ በዕለቱ ወይም በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ተገቢ ሪፖርት ወይም የሥራ አፈፃፀም ማቅረብ፤

ለ. የሥነ ምግባር ብልሹ ተግባራት ላይ ተሳታፊ አለመሆን ወይም የእምነት ማጉደል ድርጊት አለመፈጸም፤

ሐ. ከሕግ ውጭ ለሰጠው ውሳኔና አለአግባብ ጥቅም ላይ ላዋለው የቢሮን ሐብት እንደጉዳዩ ሁኔታ በተናጠልና በጋራ ተጠያቂነት እንዳለበት መገንዘብ፤

2. መርሆውንና በመርሆው ሥር የተደነገጉትን መተላለፍና የሚከተሉትን ጥፋቶች ፈጽሞ መገኘት ያስጠይቃል ወይም የእርምት እርምጃ ያስወስዳል፡-

   ሀ. የተመደቡበትንና በሥራ ኃላፊ የሚሰጥን ሕግን የተከተለ ሥራን በአግባቡ ለመፈጸም ፈቃደኛ አለመሆን፤

   ለ. የሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ በኮምፒውተር ወይም በማንኛውም መንገድ የተያዘን መረጃና ሰነድ ማጥፋት፣ መለወጥ፣ አሳልፎ መስጠት፣ በአጠቃላይ ቢሮን ወይም ሠራተኞቹን ሊጎዳ በሚችል ተግባር ላይ ማዋል፤

   ሐ. አንድን ሥራ፣ ውሳኔ ወይም ጉዳይ ያለበቂ ምክንያት እንዳይፈፀም፣ ያለአግባብ እንዲዘገይ እንቅፋት መፍጠር ወይም ሥራ እንዳይሠራ ከሚያውኩ ሰዎች ጋር መተባበር፤

   መ. ስለተከናወኑ ሥራዎች ለሚመለከተው አካል በወቅቱና ነባራዊ እውነታን መሠረት ያደረገ ሪፖርት አለማቅረብ ወይም ማብራሪያ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን፤

   ሠ. ስለተከናወኑ ሥራዎች ለሚመለከተው አካል ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት የሚያሳስት፣ ትክክል ያልሆነ ሪፖርት ማቅረብ፤

   ረ. በግዴየለሽነት ሥራን ማከናወን ወይም መምራትና ስህተትን ለማረም ጥረት አለማድረግ፤

   ሰ. በሥራ ላይ ለሌለ ሠራተኛ መመሪያ ከሚፈቅደው ውጪ ደመወዝ ወይም ማንኛውም ዓይነት ክፍያ መፈጸም ወይም መቀበል፤

   ሸ. የማኔጅመንት አባል የሆነ ሠራተኛ የማኔጅመንት ውሳኔን በተለያየ መንገድና ደረጃ ማደናቀፍ፣ ማዘግየት፣ አብሮ ሐሳብ የሰጡበትን ወይም ተሳትፎ ያደረጉበትን ውሳኔ የማኔጅመንት አባል ካልሆኑ ሠራተኞች ጋር በመሆን መተቸት፣ ማቃለል፣ ተገቢነት የሌለው አሉባልታ መንዛት ወይም ሌሎች መሰል ከመልካም ሥነ ምግባር ውጪ የሆኑ ተግባራትን መፈፀም፤

   ቀ. የማኔጅመንት አባል የሆነ ሠራተኛ አሳማኝ ምክንያት ሳይኖር ወይም የቢሮን ዋና ዳይሬክተር ወይም እና የቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቱን ዋና ሥራ አስኪያጅ ሳያስፈቅድ የማኔጅመንት ስብሰባ፣ ውይይት ወይም ሳይት ጉብኝት ላይ መቅረት፣ በተደጋጋሚማርፈድ ወይም አቋርጦ መሔድ፤

   በ. በሥራ ሰዓት ያልተፈቀዱ ስብሰባዎችን ማካሔድ ወይም ለማካሔድ ሌሎች ሠራተኞችን ማነሳሳት፤

ሀ. ቢሮ ለሚያከናውናቸው ሥራዎች ደረጃውን ወይም ጥራቱን ያልጠበቀ የእቃ ወይም አገልግሎት ግዥ እና ሌሎች መሰል ሥራዎችን ተቀባይነት እንዲያገኙ ማጽደቅ ወይም ተፈፃሚ እንዲሆኑ ማበረታታት፤

ለ. የጥቅም ግጭት የሚያስከትሉ ሁኔታዎች መኖራቸውን እያወቀ ለቅርብ የሥራ ኃላፊ ወይም ለቢሮ ዋና ዳይሬክተር ወይም ለቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ አለማሳወቅ፤

ሐ. ከቢሮ ኃላፊ ወይም ም/ቢሮ ኃላፊ ወይም ከሚመለከተው የሥራ ክፍሉ ኃላፊ ፈቃድ ውጪ የቢሮን ማንኛውም ኮምፒውተር፣ ማሽነሪ፣ መኪና፣ ፎቶ ኮፒ ማሽን እና ሌሎች የሥራ መገልገያ መሳሪያዎችን ደንበኞች ወይም ሌሎች መሰል አካላት እንዲገለገሉበት መተባበር፣ ማበረታታት፣ መፍቀድ ወይም ማድረግ፤

መ. ለደንበኞች የሚሠጥ አገልግሎትንና ውሳኔን አሳማኝ ምክንያት ሳይኖር ወቅታዊ በሆነ ሁኔታ እንዳይሰጥ ማዘግየት፣ እንዳይፈጸም እንቅፋት መፍጠር ወይም በተደጋጋሚ ማጉላላት፤

ሠ. የግል ወይም የተወሰኑ ቡድኖችን ጥቅም ከሕዝብ ጥቅም ማስቀደም፤

ረ. በሕግ የማሳወቅ ግዴታ ያለበትን ጥቅምን ሆን ብሎ አለማሳወቅ፤

ሰ. በሕግ የማሳወቅ ግዴታ ያለበትን ጥቅም በቸልተኝነት አለማሳወቅ፤

ሸ. በሕግ የማሳወቅ ግዴታ ያለበትን የራስንና የቤተሰብን ሐብት ለማስመዝገብ ፈቃደኛ አለመሆን፤

ቀ. በሕግ የማሳወቅ ግዴታ ያለበትን ሆን ብሎ ያልተሟላ ወይም ሐሰተኛ የሐብት ምዝገባ ማድረግ፤

በ. በሕግ የማሳወቅ ግዴታ ያለበትን በቸልተኝነት ያልተሟላ የሐብት ምዝገባ ማድረግ፤

ተ. በቢሮ የሥራ ሰዓት በሌላ መስሪያ ቤት ወይም ድርጅት ውስጥ ተቀጥሮ መስራት፡፡

## 14. ሕጋዊ በሆነ ስልጣን መገልገል

ሕጋዊ በሆነ ስልጣን መገልገል ማለት በሕግ ገደብና አግባብነት መሠረት በተሰጠ ስልጣን ተወስኖ የዕለት ተዕለት ሥራን ማከናወን ወይም ውሳኔን መስጠት መቻል ማለት ነው፡፡ በመሆኑም:-

1. ማንኛውም የቢሮ ሠራተኛ:-

ሀ. በሥራ ቦታ ተገቢውን ጥንቃቄና የአሰራር ስርዓት መከተል

ረ. ሥራን በተገቢው ጥንቃቄ እና ጥራት አለማከናወን ወይም በአግባቡ አለመወጣት፣

ሰ. የሥራ ኃላፊነትን መከታ በማድረግ ከበታች ሠራተኛ ወይም እና ከተገልጋዮች የግል ጥቅም መጠየቅ፡፡

15. **<u>አድልኦ አለመፈጸም</u>**

አድልዎ አለመፈፀም የቢሮ ሠራተኞች ሁሉንም ባለጉዳዮች ወይም ደንበኞች በእኩል ማየትና በመካከላቸው ልዩነትን አለመፍጠር፣ ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው የሚለውን መርህ በመከተል በቀለም፣ በዘር፣ በብሔር፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በአካባቢነት ወይም በወንዜነት፣ በኃብቻ፣ በዝምድና፣ በሌላ አቋም እና አግባብነት በሌለው ግምት ምክንያት የተለየ እንክብካቤ ወይም ልዩነት ሳያደርጉ ስራቸውን በማከናወን ፍትሐዊ አገልግሎትና ውሳኔ በመስጠት ማስተናገድ መቻል ነው፡፡ በመሆኑም፡-

1. ማንኛውም የቢሮ ሠራተኛ፡-

   ሀ. የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትና ግልፅነትን ማዕከል በማድረግ ተገቢና ፍትሐዊ በሆነ አኳኋን ውሳኔ መስጠትና ሥራውን ማከናወን አለበት፡፡ በሌላ አነጋገር በቀለም፣ በዘር፣ በብሔር፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሐይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት ወይም በሌላ አቋምና የሕግ መሠረት በሌለው ምክንያት የተለየ እንክብካቤ ወይም ልዩነት ሳያደርግ በቀረበለት ጉዳይ ፍሬ ነገር ላይ ብቻ ተመስርቶ ፍትሐዊና ሚዛናዊ የሆነ ውሳኔ መስጠት፣

   ለ. ሀገራዊና ተቋማዊ ፖሊሲን፣ ስትራቴጂን፣ አሠራርን፣ ሕግን ወዘተ በሚመለከት የምክር አገልግሎት የሚሠጥ ሠራተኛ ያለፍርሐትና ያለስጋት፣ ወገናዊ ያልሆነ፣ በቅንነት፣ በእውቀት እና በእውነት ላይ የተመሠረተ ትክክለኛ እንዲሁም ያልተዛባ ምክር መስጠት ይኖርበታል፡፡

2. መርሆውንና በመርሆው ሥር የተደነገጉትን መተላለፍና የሚከተሉትን ጥፋቶች ፈጽሞ መገኘት ያስጠይቃል ወይም የእርምት እርምጃ ያስወስዳል፡-

   ሀ. ሕገወጥ ተግባር ለመፈፀም የሕግ ሽፋን እንዲይዝ ማመቻቸት፣

   ለ. በሕግ የቅድሚያ መብት እንዲሰጥ ተለይቶ ካልተቀመጠ በስተቀር በደንበኞች ወይም በሠራተኞች መካከል የተለየ እንክብካቤ ወይም ልዩነት ማድረግ፣

   ሐ. የአንድን ጉዳይ ፍሬ ነገር መሠረት ያላደረገና አንድን አካል፣ ቡድን፣ ግለሰብ የሚጠቅም ወይም የሚጎዳ አድሏዊ ምክር መስጠት፣

2. መርሆውንና በመርሆው ሥር የተደነገጉትን መተላለፍና የሚከተሉትን ጥፋቶች ፈጽሞ መገኘት ያስጠይቃል ወይም የእርምት እርምጃ ያስወስዳል፡-

   ሀ. በቃልም ይሁን በድርጊት በሥራ ቦታ የሠራተኞችን ወይም የደንበኞችን ክብር መንካት፣ ማዋረድ ወይም ስብዕናን በሚነካ መልኩ ጥላቻን መግለፅ፤

   ለ. ሕግን፣ ሕጋዊ ትዕዛዝን፣ ተገቢነት ያለውን የአሠራር ስርዓትን አልያም ከሥራው ጋር ተያያዥነት ያለውን የመንግስት ፖሊሲ ባለመከተል እና ባለማክበር ሆን ብሎ በሥራ ላይ በደል ማድረስ ወይም ሌሎች ሠራተኞች እንዲያደርሱ መገፋፋት፤

   ሐ. ከሥራ ጋር ባልተያያዘ ጉዳይ የሌሎችን ሥራ በሚያስተጓጉል እና በሚረብሽ መልኩ ከፍተኛ ድምፅ ማሰማት፤

   መ. የቢሮን ሠራተኞች በመከፋፈል ምቹ የሥራ ሁኔታ እንዳይፈጠር ማድረግ፤

   ሠ. የቢሮ ደንበኞች ከሕግ ውጪ የተለየ ሥራ እንዲሰሩ መፍቀድ፣ እገዛ ማድረግ ወይም ማበረታታት፤

   ረ. የሥራ መግቢያና መውጫ ሠዓትን አለማክበር ወይም ለቅርብ ኃላፊ ሳያሳውቁ ወይም አሳማኝ ባልሆነ ምክንያት የሥራ ገበታ ላይ አለመገኘት፤

   ሰ. ሌሎች ሠራተኞች ሕጋዊ ትዕዛዞችን እንዳያከብሩ መገፋፋት፣ ከሕግ ውጪ እንዲሠሩ ማበረታታት ወይም እና ከህግ ውጪ ሲሠሩ ዝም ብሎ መመልከት፤

   ሸ. በሥራ ኃላፊዎች የተሠጡ ሕጋዊ የሆኑ ትዕዛዞችን ለማክበር ፈቃደኛ አለመሆን፡፡

## 17. ለደንበኞች ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ መስጠት

ለደንበኛ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ መስጠት ማለት የባለጉዳዮች ወይም የደንበኞች የአገልጋይነትን ስሜት እና ባሕሪይ መላበስ ነው፡፡ በመሆኑም፡-

1. ማንኛውም የቢሮ ሠራተኛ፡-

   ሀ. በእለት ተዕለት ከሌሎች የሥራ ባልደረቦች ጋር በሚኖር የሥራ ግንኙነት ሥራን ማዕከል ያደረገ ትብብር የማድረግ፤

   ለ. ደንበኞችን በተገቢ አክብሮትና ትህትና መቀበል፣ በጥሞና በማዳመጥ ለሚጠይቁት ጥያቄ ያልተዛባ፣ ትክክለኛ እና ወቅታዊ ምላሽ የመስጠት፤ በሌላ አነጋገር አገልግሎት ወይም ውሳኔ ፈላጊ ከሆኑ ደንበኞች ጋር የሚያደርገውን የሥራ ግንኙነት ከሚገባው በላይ በማዘግየት እና በማጉላላት አላስፈላጊ ለሆነ ወጪ ከመዳረግ መቆጠብ ወይም የሥራ ማኑዋል ወይም መመሪያ በሚያዘው መንገድ ደንበኞችን ከማስተናገድ ወደኃላ ያለማለት፤

አርዓያነትን ማሳየት፤

መ. የሌሎችን ሰዎች ሰብዓዊም ሆነ ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በማክበር የተለያዩ ሐሳቦችን የሚያስተናግድ እና የሚያደፋፍር መሆን፤

ሠ. ክብልሹ የአሰራር ስርዓት እንዲሁም የቢሮን መልካም ስምና ዝና ከሚያጎድፉ ተግባራት በመቆጠብ የአርዓያነትን ባሕል መላበስ፤

ረ. የሥራ ባልደረቦቹን መልካም ሥነ ምግባር በተላበሰ መልኩ በትህትና ማነጋገር እና ችግሮቻቸውን በጋራ መድረክ በመወያየት ማቃለል ወይም በማስረጃ ላይ የተመሠረተ ሐሳብ በማቅረብ መተማመን፤

ሰ. በቢሮ የሥራ መዋቅር ውስጥ ማንኛውም የሥራ መስክ የሚጠይቀውን የሙያ የሥነ ምግባር (Code of Ethics) በከፍተኛ ደረጃ በመከተል የተመደቡበትን ሥራ በአግባቡ፣ በጥራት፣ በታማኝነትና በፍጥነት በማከናወን የቢሮ ዓላማ እንዲሳካ ለማድረግ ቁርጠኝነት መኖር፤

ሸ. ከጊዜና ከተጨባጭ ሁኔታ ጋር ሊዳብር ለሚችል ለውጥ እራሱን ዝግጁ አድርጎ መገኘት፤

ቀ. አንድ የሥራ ኃላፊ በመምራት ሥራ እንዲሰሩ በሥሩ በቅጥር፣ በምደባ እና በመሳሰሉት የተመደቡለትን ሠራተኞች ከቢሮ ሥራ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የሀገሪቱንና የቢሮን ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ የአሠራር ስርዓቶችና መሰል ጉዳዮች ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖራቸው አስፈላጊ ገለፃዎችን በማድረግ ማስረዳት፤

በ. በየጊዜው ሙያውን ማዳበርና ተባብሮ በአንድነት የመስራት ባሕልን ማዳበር፤

ተ. ሕጋዊ በሆኑ የኮሚቴ ሥራዎች ውስጥ መሳተፍ ግዴታ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ በጀት ዓመት ውስጥ ከያዘው የሥራ መደብ በተጨማሪ በሁለት የኮሚቴ ስራዎች ውስጥ መሳተፍ የሚጠበቅበት ሲሆን በሌላ አነጋገር ከሁለት የኮሚቴ ሥራዎች በላይ እንዲሠራ አይገደድም፤

ቸ. መላ ጉልበትንና ችሎታን ለተቋሙ አገልግሎት የሚያውል፣ የኃላፊነት ስሜት የሚሰማው ሆኖ የተሻለ ለውጥን የሚደግፍ፣ ታማኝ፣ ለቢሮ መልካም ስም እና ዝና የሚቆረቆር፣ ዘመናዊ ተቋማዊ የአሠራር ባህል እንዲዳብር ብሎም የእርስበርስ መተማመን እና መከባበር እንዲሰፍን በማድረግ ቢሮ ወደ ተሻለ ደረጃ እንዲደርስ ሌት ተቀን የሚጥር መሆን አለበት፡፡

2. መርሆውንና በመርሆው ሥር የተደነገጉትን መተላለፍና የሚከተሉትን ጥፋቶች ፈጽሞ መገኘት ያስጠይቃል ወይም የእርምት እርምጃ ያስወስዳል፡-

ሀ. አንድ የሥራ ኃላፊ በሥሩ በተለያየ መንገድ ማለትም በምደባ፣ በደረጃ ዕድገት፣ በዝውውር ፣ በቅጥር እና በመሳሰሉት ለተመደቡ ወይም ለተቀጠሩ ሠራተኞች

## 21. የዲሲፕሊን ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር

በቢሮ ውስጥ የሥነ ምግባር ግድፈት ወይም ብልሹነት ሲፈፀም የዲሲፕሊን ኮሚቴ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት አሉት፡፡

1. ከሚመረምረው ጉዳይ ጋር አግባብነት ያላቸውን በቢሮ ውስጥ የሚገኙ ማንኛውንም ማስረጃዎች አስቀርቦ የመመልከት ወይም ፎቶ ኮፒ የመውሰድ ስልጣን አለው፡፡
2. በሚመረምረው ጉዳይ ላይ ጠቀሜታ ያላቸው የሰነድና ገላጭ ማስረጃዎች፣ ማስረጃው በቢሮ ውስጥ የሚገኝ ከሆነ የሚመለከተውን የሥራ ኃላፊ በማስፈቀድ፣ በሌላ መስሪያ ቤት ወይም ድርጅት የሚገኙ ከሆነ ደግሞ ጉዳዩን ለቢሮ ኃላፊ ወይም ም/ቢሮ ኃላፊ ወይም በጽ/ቤት ኃላፊ በማቅረብ በሚፃፍለት የትብብር ደብዳቤ አስቀርቦ ይመለከታል፡፡
3. የሚመረምረውን ጉዳይ ያስረዳሉ ብሎ ያመነባቸውን የቢሮ ሠራተኞችን በራሱ ጠሪነት፣ ከቢሮ ውጪ ከሆኑ ደግሞ በቢሮ በኩል ጥሪ በማስተላለፍ ቃላቸውን ይቀበላል፡፡
4. የተመራለትን ጉዳይ አስፈላጊውን ማስረጃ በመመልከት አጣርቶ የውሳኔ ሐሳብ ለቢሮ ዋና ዳይሬክተር ወይም ለቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ያቀርባል፡፡

## 22. ኃላፊነቶች እና ግዴታዎች

1. የቢሮ ሠራተኞች በዚህ መመሪያ የተቀመጡ መርሆዎችን በማይቃረን መልኩ የዕለት ተዕለት ተግባራትን የመፈፀም፤
2. የሥነ-ምግባር መኮንኑ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱት የሥነ ምግባር መርሆዎች አፈፃፀም በሚመለከት የቢሮ ኃላፊ ወይም ም/ቢሮ ኃላፊ ወይም ጽ/ቤት ኃላፊ እና ሠራተኞችን የማማከር፣ የማስተማር ብሎም በተቋሙ ስላለው የሥነ ምግባር ሁኔታ በየጊዜው ለቢሮ ኃላፊ ወይም ጽ/ቤት ኃላፊ እንዲሁም ለፌዴራል የሥነ - ምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ሪፖርት የማድረግ፤
3. የቢሮ ሠራተኞች በሌሎች ሕጎች የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ለሥነ-ምግባር መኮንኑ ትብብር መከልከል አስተዳደራዊ ተጠያቂትን እንደሚያስከትልባቸው መረዳት፤
4. በቢሮ አሰራር ላይ የሥነ-ምግባር ግድፈትን ወይም ህገ ወጥ የሆነ ድርጊትን ለሚጠቁም ሠራተኛ ድርጊቱን ሪፖርት በማድረጉ ጉዳት እንዳይደርስበት ቢሮ ጥቆማ አቅራቢውን ሠራተኛ ተገቢውን ከለላ ወይም ከማንኛውም በቀል ወይም ጥቃት የመጠበቅ፤

ይህ መመሪያ ከ….ቀን /2016 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ……ቀን/2016ዓ.ም**

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር**

**የቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ**